# ለኔ አልታይ አለኝ

እነ ሥም አይጠሬ ፤ የተዘፈነለት --- የተቅራራለቱ
ሥሙ ቢቀየርም ፤ ለውጥ አልታየበት --- ዛሬም እንደጥንቱ
አዲስአባ ሆነ ፤ ሰሜን አሜሪካ ፤ ቀድሞ የምናውቀው --- ያው የደደቢቱ
ያዳመጠ ካለ ፤ የሚናገረውን --- ቃሉን ካንደበቱ
ምሰሶ ሊሆን ነው ፤ ተንገዳግዶ እንዳይወድቅ --- የነበረበቱ
አሁንም አልጸዳ ፤ ከጎጠኞች መንደር --- ተቋጥሯል ጅራቱ ።

ተስገበገበና ፤ መለየት ተስኖት --- ጠላትን ከወዳጅ
ያሳየን ጀመረ ፤ ዘመነ ግርንቢጥ --- በሬው ሲውል ካራጅ
ቂላቂሉ በዛ ፤ ዶሮውን በቆቁ --- ለውጦ አሳዳጅ
ከጎሳ ባላባት ፤ ካገሩ ገዳይ ጋር --- መልሶ ሲወዳጅ
ወጧ እንዳማረላት ፤ ከላይ ታች ሲሮጥ --- መልሶ ሊያደራጅ
ላሰደደው ካገር ፤ አነፍናፊ ሆኖ --- ሲሆን ለሱ አጎብዳጅ
የድል ቀን ረዘመኝ ! ! ሸቅብ እንዳንወጣ--- በነ ቁልቁል ወራጅ ።

ለነሱ የታየውን ፤ ለኔ አልታይ ብሎኝ --- ተስቶኝ ካጠፋሁ
አልከራከርም ፤ እምነቴ ውድቅ ሆኖ --- ምነው በተረታሁ
ከሸንጎም አልቆምም ፤ ወንጀሌን አምኜ --- ብወድ በተቀጣሁ
በጎሳ ጥርቅም ፤ አገር ነጻ ወጥታ --- አንገቴን በደፋሁ
ሰላም ሰፍኖ ባገር ፤ መሃላ ሆኖብኝ --- ብዕሬን ባላነሳሁ ።

ታዛቢው … April 19, 2010